ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/ዳ/1470/18

ቀን፡- 22/12/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ገንዘብ ቢሮ

ባህር ዳር

ጉዳዩ፦ የተመዘገበ መመሪያ ማሳወቅን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም አንቀጽ 16(4) (በአዋጅ ቁጥር 313/2018 ዓ.ም እንደተሻሻለ) የአስተዳደር ተቋማት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎቻቸውን አዋጁ በወጣ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ፍትሕ ቢሮ በመላክ ማስመዝገብ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የአማራ ክልል ገንዘብ ቢሮ በቁጥር አብክመ/ገቢ/20 በቀን 04/12/2018 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 13/2015 ዓ/ም በክልሉ ፍትሕ ቢሮ እንዲመዘገብለት ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም እና በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ማሻሻያ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 13/2015 ዓ/ም በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 161/2018 ዓ.ም አድርጎ የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 27 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን ሲሆን መመሪያውን በክልሉ ገንዘብ ቢሮ ድረ ገፅ እንድትጭኑ በአክብሮት አሳውቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ይስማው ዘመነ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ
- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክት/ል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትህ ቢሮ

መመሪያ ቁጥር 161/2018 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ

የገንዘብ ቢሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሻሽሎ የወጣ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 283/2014 አንቀፅ 43(2) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 161/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 283/2014 የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል። በአዋጁ ትርጉም ያልተሰጣቸው በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች የሚከተለውን ትርጉም ይይዛሉ።

1) **"የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አቅራቢ"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት፣ ለሽያጭ ለማዋል የሚገዛ ወይም የሚሸጥ ማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ነው።

2) **"የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ"** ማለት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ለገቢዎች ቢሮ የሚከፈለበት ጊዜ ነው።

3) **"የተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ"** ማለት የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚመረትበት እና የሚያከማችበት ፈቃድ የተሰጠው ቅጥር ግቢ ነው።

4) **"የተፈቀደለት አምራች"** ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው በክልሉ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች የሚያመርት ሰው ነው::

5) **"ወርሃዊ ዋጋ ዝርዝር"** ማለት የተፈቀደለት አምራች ለገቢዎች ቢሮ የሚያቀርበው በሚቀጥለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚያመርታቸው ዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር ሲሆን፣ በፋብሪካው ተመርተው ለዚሁ ፋብሪካ በግብዓትነት የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችን ዋጋ ይጨምራል::

6) **"አዋጅ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሻሽሎ የወጣ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 283/2014 ነው::

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1) ይህ መመሪያ፡-

ሀ) ፈቃድ የተሰጣቸው ቢሆንም ባይሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በሚያመርቱ፣

ለ) በክልሉ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች በእጃቸው ይዞ በሚገኝ አምራች ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ወይም በማሳነስ የተከፈለባቸውን እቃዎች ይዞ በሚቀርቡ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

2) ይህ መመሪያ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ከተዘጋጀው የአሠራር ማንዋል ጋር በአንድነት መነበብ አለበት::

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለሚያመርቱ ስለሚሰጥ ፈቃድ</u>

4. <u>የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት</u>

1) ማናቸውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት::

ሀ) ማመልከቻው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት ማቅረብ አለበት::

ለ) ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፤

i. የንግድ ፈቃድና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ጨምሮ የገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ እንዲቀርቡ የሚጠይቃቸው ሰነዶች፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምዝገባ፣ ማረጋገጫና ሰነዶች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ii. አመልካቹ የሚጠቀምባቸውን የአመራረት ሂደቶች፣ እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሣሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ፣ ኮንቴይነሮች፣ መሣሪያዎች፣ መገጣጠሚያዎች፣

iii. የአሠራር ሂደቱን የሚገልጽ የጽሁፍ ማብራሪያ፣

iv. ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የማምረቻ ሕንጻ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እንዲሁም ሕንጻው፣ ክፍሎች ወይም ቦታዎች የሚገኙበትን ሁኔታ እና አካባቢውን፣

v. የእያንዳንዱን በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሣሪያ የማምረት አቅም በዝርዝር፣

vi. የማምረቻ መሣሪያዎችን ማስረጃዎች እና መግለጫዎች፣

vii. በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የዚህ ዓይነቱን ፈቃድ ለማግኘት እንዲሟሉ የሚጠበቁ መሣሪያዎችን ፣የአመራረት ሥርዓት ወይም ሌላ ተፈላጊ ሁኔታ፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መሆን አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ መሠረት ለመመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርበው፡

ሀ) በተፈቀደ ቅጽ መሠረት፣

ለ) የገቢዎች ቢሮ ከሚጠይቃቸው ሰነዶች ጋር በአንድነት መሆን አለበት።

5. <u>የማምረቻ ቦታዎችን ስለመገምገም</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና 8 መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ የገቢዎች ቢሮ የማምረቻ ቦታውን እና የአመራረቱን ሂደት ማመልከቻው ተሟልቶ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በቦታው በመገኘት መገምገም አለበት።

6. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ስለማግኘት</u>

1) የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ ሊሆን ይገባል።

ሀ) የተፈቀደለትን አምራች ስም፡

ለ) የተፈቀደለትን አምራች የግንኙነት አድራሻ (ኢሜይል፣ ፋክስ፣ ስልክ) እና ሌሎች

ሐ) ፈቃዱ ተፈጻሚ መሆን የሚጀምርበትን ቀን፣

መ) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች

የሚያመርትበትን ፋብሪካ እና የዋናው መሥሪያ ቤት አድራሻ፣

ሠ) የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ እንዲጠቀምባቸው በገቢዎች ቢሮ የተፈቀደለትን መሣሪያዎች ዝርዝር፣

ረ) የሚመርተውን ምርት ዓይነት

2) የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት በተፈቀደለት አምራች እና በገቢዎች ቢሮ መካከል እንደተፈጸመ ውል ይቆጠራል።

3) ማናቸውም ሰው ከገቢዎች ቢሮ የተሰጠ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 283/2014 የተዘረዘሩ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም።

4) በፈቃዱ የተመለከቱ የውል ቃሎችንና ሁኔታዎችን የሚጥስ የተፈቀደለት አምራች በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

5) የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተፈቀደለትን አምራች የሥራ አፈጻጸም መሠረት በማድረግ የንግድ ሥራውን የሚያካሄድባቸውን ሁኔታዎች የሚይዝ ሊሆን ይችላል።

6) የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ በተዘረዘሩ መሣሪያዎች ለመጠቀም የሚችለው በፋብሪካው በተመለከተው አድራሻ ብቻ ነው።

የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም መሣሪያ ከመለወጡ በፊት፣ ይህንኑ ለገቢዎች ቢሮ በማስታወቅ በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ መጠየቅ አለበት።

7) የተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ እና የማምረቻ መሣሪያዎች በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟሉ መሆኑ በገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎች ጉብኝት ሳይረጋገጥ የኤክሳይዝ ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም።

8) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም የመሳሪያዎች መለወጥ ለገቢዎች ቢሮ ሳያስታውቅ እና በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ ሳይደረግ አድራሻውን ወይም መሳሪያዎችን የለወጠ ባለፈቃድ በአዋጅ አንቀጽ 38 መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

7. **ፈቃድ ስለመስጠት**

1) አመልካቹ ያቀረበው ማመልከቻ ከተመረመረ እና የማምረቻ ቦታው በገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎች ከተገመገመ በኃላ መስፈርቶቹ መሟላታቸው ሲረጋገጥ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ይሰጣል።

2) የተፈቀደለት አምራች በአመራረቱ ሂደት ወይም ሌላ ማናቸውም ፈቃዱ በተሰጠበት ሁኔታ ላይ ለውጥ ማድረግ በሚፈለግበት ጊዜ አስቀድሞ ለገቢዎች ቢሮ ማስታወቅ እንዲችል በፈቃዱ ላይ የሚመለከተው የገቢዎች ቢሮ አድራሻ መመልከት አለበት።

8. **አዲስ አምራቾች**

1) በአዋጁ መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ያልተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚፈልግ ሰው የማምረት ስራውን ለመጀመር ካቀደበት ቀን 30 ቀን በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ለገቢዎች ቢሮ ማመልከት አለበት።

2) የማመልከቻው ቅጽ አዲስ የሚጀመረው የንግድ ስራ በሚመለከት የተሟላ መረጃ ማግኘት የሚያስችል መሆን አለበት፣ በተለይም የንግድ ስራው የሚመሩ ኃላፊዎች፣ የሚመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት አይነት፣ የማምረቱ ተግባር የሚከናወንበት ቦታ፣ የግብዓቱን ዓይነት፣ የግብዓት ምርት ጥምርታውን እና የማምረቻ መሳሪያውን አይነት የሚያካትት መሆን አለበት

3) የማምረቻ ቦታው በገቢዎች ቢሮ ከመጎብኘቱ እና አመልካቹ የማመልከቻውን ቅጽ በሚገባ ሞልቶ ከማቅረብ በፊት ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም።

9. **ተጨማሪ ፋብሪካ ስለማቋቋም**

1) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ላይ ያልተመለከተ አዲስ ፋብሪካ ለማቋቋም ያቀደ እንደሆነ በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ወይም አዲስ ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ አለበት።

2) ማናቸውም ሰው የገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎች የማምረቻ ቦታውን ጎብኝተው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት መጀመር አይችልም።

በአማራ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

3) ፈቃድ ባልተሰጠው ፋብሪካ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርት ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ መሰረት አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ይቀጣል።

10.የኤክሳይዝ ፈቃድ ወይም ምዝገባ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

1) በአዋጅ አንቀጽ 19 ከተመለከተው በተጨማሪ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የገቢዎች ቢሮ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው የኤክሳይዝ ፈቃድን ማገድ ይችላል።

ሀ) ከአምራቹ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በተፈቀደለት አምራች የተመረተ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤

ለ) የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ወይም በምዝገባው ከተመለከተው ውጪ በሆኑ ተግባራት ተሠማርቶ የተገኘ እንደሆነ፤

ሐ) ፈቃድ የተሰጠበት ተግባር በአዋጁ ወይም በሌላ ሕግ የተከለከለ እንደሆነ፤

መ) የተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም መሳሪያ ከገቢዎች ቢሮ ፈቃድ ውጪ ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ ፤

2) በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ የታገደ እንደሆነ ባለፈቃዱ

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም እና

ለ) የገቢዎች ቢሮ በሚያቀርባቸው ሁኔታዎች መሰረት መፈጸም አለበት።

3) በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ወይም ምዝገባ የተሰረዘ እንደሆነ፦

ሀ) ባለፈቃዱ፦

i. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ተግባሩን ማቆም

ii. በእጁ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል

iii. የገቢዎች ቢሮ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ መሳሪያዎች፣ ቁሳቁሶች መሸጥ አለበት።

ለ) የገቢዎች ቢሮ

i. የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ ሌላ ቦታ እንዲያዘዋውር

ii. የመንግስትን ገቢ ለመሰብሰብ እና አዋጁን ለማስፈጸም እንዲቻል የተፈቀደለትን አምራች በፋብሪካ በቁጥጥር ስር ለማድረግ ይችላል።

4) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ፋብሪካን በቁጥጥር ስር ማድረግ" ማለት በፋብሪካው ውስጥ የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነው ማናቸውም ተግባር በገቢዎች ቢሮ ፈቃድና አውቅና እንዲከናወን ማድረግ ነው።

ክፍል ሦስት

የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር

11.በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ

1) የተፈቀደለት አምራች

ሀ) ገቢዎች ቢሮ በሚጠይቀው መሰረት በማምረቻ ቦታው ዋና የመግቢያ በር እና በሌላም አስፈላጊ ቦታ ላይ በአማርኛና በአካባቢው የስራ ቋንቋ:-

I. "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ" እና

II. የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ፅሑፍ መለጠፍ አለበት።

ለ) ምርቱ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተላለፊያ መስመሮች በቋሚነት የተገጠሙ እና መላውን ርቀት በትክክል ለመመርመር የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

ሐ) የማከማቻ እና የማሰተላለፊያ መስመሮች ኢንዱስትሪው የሚጠይቀውን ደረጃ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

መ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሚመረቱባቸው፣ ለሽያጭ በሚዘጋጅባቸው ወይም በሚከማቹባቸው መሳሪያዎች ላይ በዘይት ቀለም ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

ሠ) ለተፈቀለት አምራች የገቢዎች ቢሮን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሳሪያ ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሳሪያ የተገጠመባቸው እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

ረ) ለኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ ሲባል መቆለፍ ወይም ማሸግ እንዲቻል የገቢዎች ቢሮ በሚጠየቀው መሰረት መሳሪያዎችን ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ሰ) የገቢዎችን ቢሮ በሚያረካ ሁኔታ:-

I. በእያንዳንዱ የማምረት ሂደት የምርት ርክክብ የሚፈፀምባቸው የማሰተላለፊያ መስመሮች በተለያዩ የዘይት ቀለም እንዲቀቡ እና ቀለሙ እንዳይጠፋ በየጊዜው እንዲታደስ ማድረግ አለበት፡፡

II. ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች ሁኔታ እያንዳንዱ ማከማቻ ወይም መሳሪያ ማሰቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያሰችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሳሪያ መግጠም አለበት፡፡

ሸ). ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሰ) አፈፃፀም የማጣሪያ ፋብሪካ ባለቤት በተሟላ አኳኋን እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መንገድ የማስተላለፊያ መስመሮችን የሚከተለውን የዘይት ቀለም ዓይነት መቀባት አለበት፡፡

I. የአልኮል መጠጥ - ቀይ

II. ቢራ - ሰማያዊ

III. ሞላሰስ - አረንጓዴ

IV. የሚጣራ ወይን - ቡናማ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ
The ANRS Bureau of Justice
የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

V. ውሳ - ቢጫ

VI. ናፍጣ - ጥቁር

ቀ) ለገቢዎች ቢሮ አስቀድሞ በማሰታወቅ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር የአመራረቱን ሂደት ወይም አካሄዱን መለወጥ፣ ማከማቻ ወይም መሳሪያ መጨመር፣ የለበትም።

2) የተፈቀደለት አምራች

ሀ) በተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ የፅሕፈት ስራ የሚያከናውንበት ቢሮ፣ የማምረቻው ቦታ፣ የጥሬ ዕቃ መጋዘን፣ የምርት መጋዘን የተለያየ መሆን አለባቸው።

ለ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) አፈፃፀም ለእያንዳንዱ ተግባር የተመደበው ቦታ ጥበቃ የሚደረግለት እና አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስን በሚገባ መሰብሰብ እንዲቻል ለይቶ ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ የሚያስችል አካል የተገጠመለት መሆን አለበት።

3) ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የተፈቀደለት አምራች ዕቃዎች የሚያከማችበት በገቢዎች ቢሮ የተፈቀደ የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል።

12. <u>ፋብሪካውን በሩቅ መቆጣጠር የሚያስችል መሳሪያ ስለመግጠም</u>

1) የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወነውን እንቅስቃሴ በሩቅ ማየት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ስርዓት መግጠም አለበት።

2) የገቢዎች ቢሮ በዚህ መመሪያ መሰረት ሊገጠም የሚገባውን የቴክኖሎጂ መሳሪያ ዝርዝር ባህሪያት ይወስናል።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም የገቢዎች ቢሮ ፋብሪካውን በሩቅ ማየት የሚያስችለውን የቴክኖሎጂ ስርዓት የመጠቀም ያልተገደበ መብት ይኖረዋል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) የተመለከተው የቴክኖሎጂ ስርዓት የገቢዎች ቢሮ በሚጠይቀው መሰረት ደህንነቱ የተጠበቀ የምስል ማከማቻ እና ምስልን እና ሌላን መረጃ በዲጂታል ስርዓት በቀጥታ ማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት።

በአማራ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

13.የአመራረት ሂደት በቴክኖሎጂ ስለማስደገፍ

1) የገቢዎች ቢሮ የተወሰኑ የተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች በእያንዳንዱ ደረጃ ያሏቸው የአመራረት ሂደት በአውቶማቲክ የአመራረት ሂደት የታገዘ እንዲሆን ሊጠይቅ ይችላል።

2) የአልኮል መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካዎችን በሚመለከት ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ግዴታ ሊጣልባቸው የሚችለው የፋብሪካው የማምረት አቅም በሰዓት ከ500 (አምስት መቶ) ጠርሙስ በላይ ሲሆን ነው።

14.የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሳሪያዎች

1) የገቢዎች ቢሮ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት በማምረቻ ቦታዎች ሊተክሉ የሚገባ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ እንዲሁም ሌሎች መሳሪያዎችን ተፈላጊ ባህሪያት በጋዜጣ እና በድረገፅ ላይ መሰራጭት አለበት።

2) በገቢዎች ቢሮ የሚፈቀዱት በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሳሪያዎች የጥሬ ዕቃዎችን፣ የግብዓቶችን እና የአላቂ ዕቃዎችን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው።

3) የጥሬ ዕቃ እና የአላቂ ምርቶች ማከማቻ ጋኖች በጋኑ ውስጥ ያለውን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ስርዓት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

4) በዚህ መመሪያ መሰረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሳሪያዎች የገቢዎች ቢሮ በሚወሰነው መሰረት በምርቱ ሂደት በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ላይ መገጠም አለባቸው።

5) የተፈቀደለት አምራች:-

ሀ) የገቢዎች ቢሮ ለሚያካሂደው ቁጥጥር እና ስሌት በሚያመች መንገድ መቁጠሪያ እና መለኪያ ያላቸውን ጋኖች ወይም ማከማቻዎች የማዘጋጀት፣ በትክክል የሚሰሩ መሆኑን በየጊዜው የማረጋገጥ፣ እና

ለ) በመለኪያ እና በመቁጠሪያ መሳሪያዎች ላይ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ የተደረገውን ዕድሳት የሚያሳይ መዝገብ የማዘጋጀት፣ መሳሪያዎቹ በትክክል የሚሰሩ መሆኑን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

15.በምርቶች፣ በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት (ሌብል) ስለማድረግ

1) ከታክስ ነፃ የሆኑ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማሸጊያዎች ለመከታተል እና ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል አኳኋን የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል።

2) ለጅምላ ሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችን የሚይዝ እያንዳንዱ ማሸጊያ ወይም መያዣ ወይም መጠቅለያ በሚከተለው አኳኋን ህትመት ሊደረግበት ይገባል:-

ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ፣ የመጨረሻ መድረሻውን አገር የሚያሳይ ፅሑፍ፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል የሚል ፅሑፍ፣

ሐ) ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ለሚሸጡበት መደብር ወይም ለዲፕሎማቲክ ሱቆች የሚሸጥ ከሆነ ከታክስ ነፃ የሚል ፅሑፍ፣

3) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የገቢች ቢሮ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ዕቃዎችን ለመለየት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ምልክት በመመሪያ ሊወሰን ይችላል።

16. በጥሬ ዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች መጠናቸውን በትክክል ለማወቅ ለሚደረገው ቁጥጥር በሚያመች አኳኋን ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል ወይም መጋዘን መቀመጥ አለባቸው።

2) በተፈቀደለት ማምረቻ ውስጥ ለምርት ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ወይም አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በገቢዎች ቢሮ ሳይፈቀድ ጥሬ ዕቃዎችን ማውጣት አይችልም።

3) የአልኮል ማጣሪያ ባለቤት ከኤቴል አልኮል በስተቀር ማናቸውንም ሌላ አልኮል በገቢዎች ቢሮ በሚወሰነው መሰረት ለሰው ጥቅም እንዳይውል ከመደረጉ በፊት በመጋዘን ማስቀመጥ አይቻልም።

17.የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማሰረከብ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የማምረት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ" በመባል ወደ ሚታወቅ ክፍል

መዘዋወር እና በዚህ መመሪያ መሰረት ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውጪ እስከሚደረጉ ድረስ በዚሁ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው። ሆኖም የተጣራ አልኮል መቀበያ ጋኖች የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ እንደሆኑ ይቆጠራል።

2) የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል በር ላይ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል" የሚል ዕሑፍ መለጠፍ አለበት።

3) የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የተመረቱ ዕቃዎች ከማከመቻነት ውጪ ለሌላ ለማናቸውም ተግባር እንዲውል ማድረግ አይችልም።

4) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ለቆጠራ በሚያመች አኳኋን በኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

5) ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት ዕቃ መያዣ ጠርሙስ ወይም ማሸጊያ አምራቹን ለይቶ ማወቅ የሚያስችለው ልዩ ምልክቱ (ሌብል)፣ የአምራቹ ስም፣ የተመረተበት ቦታ እና ቀን፣ አድራሻው፣ የተከታታይ ምርት ቁጥር፣ የባር ኮድ ወይም ሌላ ተጨማሪ ምልክት ሳይደረግበት በፊት ከኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ማውጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ወይም መፍቀድ የለበትም።

6) ለውጭ ገበያ ወይም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ሊሸጡ የተመረቱ ዕቃዎች ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች መንገድ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው።

7) የተፈቀደለት አምራች ከተሸጡ በኋላ ወደ ተመረቱበት ፋብሪካ የተመለሱ ዕቃዎች የሚቀመጡበት የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል።

18. <u>ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ከታክስ ነፃ ሆነው የሚሸጡ ዕቃዎች</u>

1) የተፈቀደለት አምራች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካጋጠሙ በዕቃዎቹ ላይ ታክሱን እንዲከፍል ይገደዳል:-

ሀ) ለውጭ ገበያ የተመረቱ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተሸጡ እንደሆነ፣

ለ) ከታክስ ነፃ ሆነው ስለሚሸጡበት ወይም ታክሱ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ በአዋጅ የተመለከተው ያልተሟላ እንደሆነ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

2) የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና የተከፈለባቸው ታክስ ተመላሽ የሚደረግ ዕቃዎችን የማስታወቅ እና ማጓጓዝ ኃላፊነት አለበት።

3) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ የአልኮል መጠጦችን የሚሸጥ የቀረጥ ነፃ መደብር እነዚህን ዕቃዎች ወደ አገር ለማስገባት የሚችለው "ከቀረጥ ነፃ" የሚል ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን ብቻ ነው።

19. <u>የሂሳብ መዝገብ ስለመያዝ</u>

1) የተፈቀደለት አምራች በታክስ አሰተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2010 ድንጋጌዎች መሰረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት መያዝ ያለበት የሂሳብ መዝገብ፣

ሀ) በሚነበብ እና ሊጠፋ በማይችል አኳኋን በፅህፈት መሳሪያ የተዘጋጀ፣ የታተመ ወይም የተባዛ ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ ከመፅደቁ በፊት የተደረገ እርማት ወይም ለውጥ ሲኖር የተደረገውን ለውጥ ወይም እርማት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል፣ እርማቱን ያከናወነነው ሰው ፊርማ እና የታረመበት ቀን የተባዛበት፣

ለ) በተፈቀደ አኳኋን በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መንገድ የተዘጋጀ እና በተፈቀደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር ለውጥ ያልተደረገበት፣ መሆን አለበት።

3) የገቢዎች ቢሮ በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ውጪ የተዘጋጀን የሂሳብ ሰነድ ወይም ማስረጃ ላለመቀበል ወይም በዚህ ሰነድ መሰረት ስራዎችን ላለማከናወን ይችላል።

4) የገቢዎች ቢሮ ማናቸውም የሂሳብ ሪፓርት ሊቀርብ የሚገባበትን ቅጽ ወይም ለአዋጁ እና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተቀባይነት የሚኖራቸውን ሰነዶች ዓይነት ሊወሰን ይችላል።

20. <u>ልዩ ምልክትን (ሌብል) ስለማሳወቅ</u>

1) ማናቸውም የተፈቀደለት ሰው በተፈቀደው ቅጽ መሰረት እና የገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው እና በሚያጸድቀው ዝርዝር መሰረት ልዩ ምልክቱን ሳያስታውቅ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ለሽያጭ በጠርሙስ ወይም በሌላ መያዣ ማሸግ አይችልም።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የገቢዎች ቢሮ ማመልከቻ ሲቀርብለት ሁኔታዎችን በመወሰን የተፈቀደለት አምራች ለሙከራ የሚውሉ ምርቶችን እንዲያመርት ሊፈቅድ ይችላል።

21.<u>የምርት መከታተያ ስርዓት</u>

1) የገቢዎች ቢሮ የተፈቀደለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች የምርት ሂደቱን መከታተል የሚያስችል የሂሳብ ስርዓት እንዲዘረጋ ሊያዝ ይችላል።

2) የምርት መከታተያ ስርዓት:-

ሀ) የምርት ትክክለኛነት የማረጋገጥ ወይም ማሳየት የሚያስችል መሳሪያ፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን በተፈቀደለት አምራች የተመረቱ ዕቃዎችን ብዛት ለመቆጣጠር፣ ለመመዝገብ እና መረጃውን ለማስተላለፍ የሚያስችል መሳሪያ፣ መሆን አለበት።

3) የምርት መከታተያው ስርዓት በማምረቻው ቦታ በምርት ስንሰለት ውስጥ በእያንዳንዱ የማሸጊያ ወይም የማተሚያ መሳሪያ ላይ ሊገጠም ይገባል።

4) አዲስ ወይም የተሻሻለ የምርት መከታተያ ስርዓት መግጠም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ የገቢዎች ቢሮ ለአምራቹ መሳሪያው ከሚገጠበት ጊዜ በፊት የሚከተሉትን የያዘ ማስታወቂያ መሰጠት አለበት:-

ሀ) አዲሱ መሳሪያ የምርት መከታተያውን ስርዓት የተሻለ ለማድርግ አስፈላጊ መሆኑን፣

ለ) በእያንዳንዱ የምርት ስንሰለት ውስጥ የሚደረገውን የማስተካከያ ስራ ባህሪያት፣ እና

ሐ) በኮፒውተሮች እና ሌሎች መሳሪያዎች ላይ መሳሪያው የሚገጠምበትን እና የሚሰራበትን ሁኔታ፣

5) የተፈቀደለት አምራች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይስሩ የምርት መስመሮች በሚከተለው አኳኋን ለገቢዎች ቢሮ ማስታወቅ አለበት:-

ሀ) የማይሠሩ መስመሮችን በ24 ስዓት ውስጥ፣ ወይም

ለ) አምራቹ ምርቱን ከ2 ስዓት በላይ የሚያቋርጥ ከሆነ የምርት ሂደቱ በተቋረጠ በ24 ስዓት ጊዜ ውስጥ

6) የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የገቢዎች ቢሮ የምርት መስመሮችን መቆጣጠር አለበት:-

ሀ) የተፈቀደለት አምራች በዚህ አንቀጽ መሰረት የምርት መስመሮች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሰሩ መሆኑን ካሳታወቀ፣ ወይም

ለ) የምርት መስመሮች የማምረት አቅም ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ፣

7) የገቢዎች ቢሮ በዚህ መመሪያ መሰረት የምርት መስመሮችን እየተቆጣጠረ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት አምራች የታሸገው የምርት መስመር እንዲከፈትለት ለማድርግ አምራቹ ማምረት የሚጀምርበትን ቀንና ሰዓት ጭምር ያያዘ የአመራረቱን የጊዜ ሰሌዳ የሚያሳይ ሪፓርት ለገቢዎች ቢሮ ማቅረብ አለበት።

ክፍል አራት

የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ስለማከናወን -በዋጋው በመቶኛ

22.የኤክሰሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋምበት ጊዜ

1) ሽያጭ የተከናወነ ቢሆንም ባይሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች ከተመረቱበት የተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ በወጡበት የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል።

2) በገቢዎች ቢሮ የተፈቀደው የብክነት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ ማብራሪያ ወይም ማስረጃ ሊቀርብባቸው ያልቻለ በቆጠራ ጊዜ ያልተገኙ ወይም የጠፉ ዕቃዎች በአዋጅ ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል።

23. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት ስለሚሆን ዋጋ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በዕቃው ዋጋ ላይ ተመስርቶ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረው:-

ሀ) ለገቢዎች ቢሮ በእያንዳንዱ ወር ከ30ኛው ቀን በፊት በሚቀጥለው ወር ከፋብሪካው የሚወጡ ዕቃዎች የሚቀርበው ዋጋ ዝርዝር ይሆናል።

ለ) ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ለእያንዳንዱ ምርት ዓይነት፣ መያዣ እና የመያዣ ዓይነት የሚኖረውን ዋጋ የሚያመለክት መሆን አለበት።

ሐ) ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የሚሆነው ምርቱን ወደ ገዢው ለማድረስ የሚወጣውን የትራንስፓርት ሂሳብ የሚጨምር አይሆንም፣

መ) በአዋጅ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢዎች ቢሮ ምርቱ የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልበት ወደ ገበያ መቅረቡን ወይም ታክስ ከፋዩ የገለፀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ዋጋውን ይወሰናል።

ሠ) በአዋጅ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሰረት የገቢዎች ቢሮ ትክክለኛ ዋጋን መሰረት በማድረግ የሚከፈለውን ታክስ የሚወሰነው ታክስ ከፋዩ ያስታወቀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች ከሆነ፣ ምርቱ ታክስ ሳይከፈልበት ለገበያ ከቀረበ፣ ወይም ምርቱ ፈቃድ በሌለው ሰው የተመረተ በሚሆንበት ጊዜ ነው።

ረ) ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረውና ለኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መሰረት የሚሆነው ሌላ የተፈቀደለት አምራች ለተመሳሳይ ዕቃዎች የሚያስከፍለው ዋጋ ሊሆን ይችላል።

ሰ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከመያዣው ጋር አብሮ የሚሸጥ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በጠቅላላው ዋጋ ላይ ይሆናል። ሆኖም መያዣው ተመላሽ የሚደረግ ከሆነ በመያዣው ዋጋ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልም።

ሸ) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የመጨረሻ ምርቶች ለማምረት የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የሚያዘጋጀው የዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር የእነዚህን ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ የሚጨምር መሆን አለበት። ስለሆነም የንዑስ አልኮል በሊትር የሚኖረው ዋጋ እና የትምባሆ ቅጠል በኪሎ ግራም የሚኖረው ዋጋ በዝርዝሩ ውስጥ መካተት ይኖርበታል።

24.ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቅራረብ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወንበት ዋጋ ግልፅ እንዲሆን እና አምራቾች በእኩል መወዳደር እንዲችሉ እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች የምርቱን ዋጋ ዝርዝር በምርት ዓይነት፣ በመያዣው መጠን

እና ዓይነት እንዲሁም ለገበያ በሚውልበት ቦታ በመለየት ለገቢዎች ቢሮ በየወሩ ማቅረብ አለበት።

2) ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር የሚዘጋጅበትና የሚቀርብበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቶች በተዘጋጀው ማንዋል ውስጥ በዝርዝር ይመለከታል።

3) የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት፣ የነጠላውን መጠን እና ዓይነት የሚያሳየው የዋጋ ዝርዝር የእያንዳንዱን ምርት የማምረቻ ወጪ እና የትርፍ ህዳግ የያዘ ሊሆን ይገባል።

4) ዕቃው ለገቢዎች ቢሮ በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በላይ የተሸጠ እንደሆነ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የሚሆነው በደረሰኙ ላይ የተመለከተው ዕቃው የተሸጠበት ትክክለኛ ዋጋ ይሆናል።

5) ዕቃውን ለገቢዎች ቢሮ በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በታች የተሸጠ እንደሆነ ወይም ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ዋጋው ያልተከፈለበት ከሆነ ከፋብሪካው በወጣው ዕቃ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በቀረበው የዋጋ ዝርዝር በተመለከተው ዋጋ መሰረት ይሆናል።

6) ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና /ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል።

ሀ) ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበት ቀን፣

ለ) የእቃውን ማስረከቢያ ቦታ፣

ሐ) የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ የሚወጣ ከሆነ ይህንኑ፣

መ) ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ ይህንኑ፣

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት፣

ረ) የእቃዎችን ብዛት፣

ሰ) የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ዋጋ፣

ሸ) ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ፣

25.የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ

1) የእያንዳንዱ ወር የኤክሳይዝ ታክስ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ያለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለገቢዎች ቢሮ መቅረብ አለበት።

2) የተፈቀደለት አምራች ታክሱን የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ባለው 30 ቀን ጊዜ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክሱን ለገቢዎች ቢሮ ገቢ ማድረግ አለበት።

3) ከዋጋ ዝርዝር፣ ከማስረከቢያ ሰነድ እና ከደረሰኝ ጋር ማመሳከር እንዲቻል በኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ውስጥ የእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ዓይነት እና ለሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሳይሸጥ የተመለሰው ተለይቶ ማስታወቂያ ሊቀርብበት ይገባል።

4) የገቢዎች ቢሮ በእያንዳንዱ የታክስ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተውን መረጃ በተፈቀደለት አምራች ከሚያዘው የምርት፣ በመጋዘን የሚገኝ ዕቃ እና የሽያጭ መረጃ ጋር ማመሳከር አለበት።

5) የተፈቀደለት አምራች የታክስ ማስታወቂውን ትክክለኛነት የሚያስረዱ ደረሰኞችን፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶችን እና የየእለቱን የኤክሳይዝ ታክስ መረጃ በሚገባ መያዝ አለበት።

6) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ መረጃዎችን በሚገባ ያልገባ /ያልያዘ እንደሆነ በአዋጁ እንቀጽ 38 መሰረት በወንጀል ተጠያዊ ከሆኑ በተጨማሪ ካልተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እጥፍ የሆነ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃዱን የመሰረዝ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል።

26.የዕቃ ቆጠራ እና የጠፋ ዕቃዎች

1) እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ጨምሮ በፋብሪካው ውስጥ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ በየዓመቱ የተሟላ ቆጠራ ማካሄድ አለበት።

2) ከዚህም በተጨማሪ የተፈቀደለት አምራች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ ተከታታይነት ያለው ወርሃዊ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፦

ሀ) በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኘውን ጥሬ ዕቃና የመጨረሻ ምርት፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

ለ) አዲስ ወደ ፋብሪካው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን፣

ሐ) በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችን፣

መ) በፋብሪካ የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶችን፣

ሠ) በፋብሪካው ተመርተው ወደ ፋብሪካው መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን

ረ) የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሰ) የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሸ) የገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎችን፣

3) የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት።

4) ዕቃዎች የጠፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የዕቃው መጥፋት በታወቀበት ጊዜ ወዲያውኑ ሪፓርት የተደረገና አግባብ ባለው የፀጥታ አካል ምርመራ ተካሂዶ የዕቃው መጥፋት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን መጥፋቱ ባልተረጋገጠ ዕቃ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል።

5) በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ቆጠራ ከመካሄዱ ከ14 ቀን በፊት የገቢዎች ቢሮ ይህንኑ እንዲያውቀው ማደረግ አለበት።

6) ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ በፋብሪካው ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የስራ እንቅስቃሴ መቆም አለበት።

ክፍል አምስት

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች

27.በተፈቀደለት አምራች የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ

1) የተፈቀደለት አምራች የመጨረሻውን ምርት ለማምረት የሚጠቀምባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ራሱ የሚያመርት እና የኤክሳይዝ ታክሱ ስሌት በዋጋው በመቶኛ በሚሆንበት ጊዜ የጥሬ ዕቃው ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ነው።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

2) ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው ጥሬ ዕቃውን ለማምረት የሚወጣው ወጪ እና ጥሬ ዕቃው ለሶስተኛ ወገን ቢሸጥ የሚታለውን የትርፍ ህዳግ የሚያጠቃልል ይሆናል።

3) የተፈቀደለት አምራች ጥሬ ዕቃውን ለሶስተኛ ወገን ጭምር የሚሸጥ ከሆነ፣ ለሶስተኛ ወገን የሚሸጠበት ዋጋ የመጨረሻውን ምርት ለሚያመርተው ፋብሪካም ጥሬ ዕቃው የተሸጠበት ዋጋ እንደሆነ ይቆጠራል።

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚወሰነው የእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃ ዋጋ የተፈቀደለት አምራች በሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ መካተት አለበት።

ክፍል ስድስት

በቁርጥ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች መጠን አወሳሰን

28. በብዛት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው

1) በመደበኛ ሁኔታ በብዛት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሰላው በዕቃው ማሸጊያ ላይ የተመለከተውን ብዛት መሰረት በመድረግ ይሆናል።

2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ እንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማሸጊያው ላይ ከተመለከተው በላይ ሆኖ ከተገኘ፣

ሀ) ዕቃው ውርስ እንዲደረግ፣

ለ) በተጨማሪው ዕቃ ላይ ወዲያውኑ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል፣

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት ቅጣት እንዲጣል፣

ሊወሰን ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ተጨማሪውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል ወይም ቅጣት እንዲጣልበት የሚደረገው አምራቹ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ይዞ የተገኘው ሰው እና አምራቹ በአንድነት እና በነጠላ ሊሆን ይችላል።

በአማራ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀትና ማጠናቀት ዳይሬክቶሬት

ክፍል ሰባት

በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች መጠቀምን ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ማስረጃ

29.የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ስለመጠቀም

1) በአዋጁ በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ተጠቅመው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርቱ አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍሉ የተፈቀደ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት አምራች ጥሬ ዕቃው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ እርሻ የተመረተ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

2) ጥሬ ዕቃው በአገር ውስጥ የተመረተ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርበው መረጃ የማስረከቢያ ሰነድ፣ ደረሰኝ፣ ከአምራቹ ጋር የተደረገ ውል እንዲሁም የአምራቹን ስም እና አድራሻ ይጨምራል።

3) የተፈቀደለት አምራች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ ካልቻለ ከውጭ አገር በሚመጣ ግብዓት ለሚመረቱ የተወሰነው የማስከፈያ ምጣኔ ተፈፃሚ ይደረጋል።

ክፍል ስምንት

የምርት ብዛት ልኬት

30. የተመረተው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት ስለመመዝገብ -ጠቅላላ

1) የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወነው በዋጋው በመቶኛ ወይም በቁርጥ ወይም በሁለቱም ቢሆንም የተመረተው ምርት ብዛት በትክክል ሊመዘገብ እና ሪፓርት ሊደረግ ይገባል።

2) በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ወይም ለማከማቸት የሚውሉ መሳሪያዎች ወይም የማምረቻና የማከማቻ ቦታዎች የዕቃዎቹን ብዛት እና ዓይነት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል የመቁጠሪያ መሳሪያ ያላቸው መሆን አለባቸው።

3) በእያንዳንዱ ፋብሪካ በምርት ሂደት ሊያጋጥም የሚችለው ተቀባይነት ያለው የብክነት መጠን በገቢዎች ቢሮ ይወሰናል።

31. የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት ስለመለካት

1) የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት የሚለካው በሁለት ቁልፍ ደረጃዎች ይሆናል፣እነዚህም፦

ሀ). በምርት ሂደት ውስጥ ፈሳሹ በጥቅል ተከማችቶ በሚገኝበት ጊዜ፣

ለ). ፈሳሹ በሚታሸግበት ጊዜ፣

2) ማናቸውም የተፈቀደለት አምራች በጥቅም ተከማችቶ የሚገኘው ፈሳሽ እና የታሸገው ፈሳሽ ብዛት እስከተቻለ ድረስ እኩል መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

3) ፈሳሽ ምርቱ በማሸግ ሂደት የሚባክነው መጠን ተመዝግቦ መያዝ አለበት።

4) የተፈቀደለት አምራች የማሸግ ተግባር ከመከናወኑ በፊት እና ከተከናወነ በኋላ ፈሳሹን የሚለካ አስፈላጊው ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሳሪያ በፋብሪካው ውስጥ መግጠም እና የመሳሪያውን ንባብ በየጊዜው መወሰድ አለበት።

5) ማናቸውም የተፈቀደለት አምራች ፈሳሽ የሚለካውን ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሳሪያ ትክክለኛነት በየጊዜው ማስመርመር እና የገቢዎች ቢሮ በሚጠይቅበት ጊዜ የምርመራው ውጤት እንዲሰጠው ማድረግ አለበት።

6) ፈሳሽ 10 ሊትር ወይም በታች በሆነ ቆርቆሮ ፣ጠርሙስ ወይም ሌላ አነስተኛ ማሸጊያ በሚታሸግበት ጊዜ የገቢዎች ቢሮ የኤክሳይዝ ታክሱ በእያንዳንዱ ማሸጊያ ውስጥ ባለው ፈሳሽ ትክክለኛ መጠን ላይ ተመስርቶ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የተፈቀደለት አምራች የሚጠቀምበት ብዛትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ የአማካኝ ይዘት ከሆነ የታሸገው ፈሳሽ አማካኝ ይዘት በቆርቆሮው ወይም በጠርሙስ ወይም በህትመቱ ወይም በብረት በርሜል ወይም በእንጨት በርሜል የታሸገ በሚሆንበት ጊዜ በደረሰኙ ወይም በማሰረከቢያው ሰነድ ላይ ከተመለከተው ያነሰ ሊሆን አይችልም።

8) የአማካኝ ይዘት ዘዴ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ በጥቅል የተያዘው ፈሳሽ ልኬት፣ ቀጥሎም የታሸገበት ዕቃ ብዛት፣ የማሸጊያው ልክ በትክክል መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ልኬት ከ2% ያልበለጠ ብክነት ሊኖር እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባት የታሸገው ምርት በጥቅል ከተያዘው ፈሳሽ ጋር እኩል መሆኑን መሳየት አለበት።

9) እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በፈሳሽ ማከማቻው የተያዘው ፈሳሽ ብዛት ወደ ማሸጊያ ከተላለፈው ብዛት ያልበለጠ መሆኑን ለማረጋገጥ በማሸጊያዎች የመሙላቱ ሂደት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ አለበት።

10) የተፈቀደለት አምራች የገቢዎች ቢሮ ለሚከናውነው የክትትል ስራ አጋዥ እንዲሆን በቁጥጥር ስራው የተገኘውን ውጤት መመዝገብ እና ሪፓርት ማድረግ ይኖርበታል። በተደጋጋሚ ከመጠን በላይ ፈሳሽን የመሙላት ተግባር መከናወኑን የሚያሰረዳ ማስረጃ ያለ እንደሆነ የተፈቀደለት አምራች ተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገዳዳል።

ክፍል ዘጠኝ

የአልኮል ጥንካሬን ስለመለካት

32.የአልኮል ጥንካሬ መለካት-በማብላላት የሚመረት

1) የአልኮል መጠጦችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የአልኮል ጥንካሬውን መሰረት በማድረግ ከሆነ የእያንዳንዱን ምርት የአልኮል ጥንካሬ መለካት አለባቸው።

2) የተፈቀደለት አምራች የሚገኘው ውጤት ከዚህ በታች በተመለከተው ዘዴ ተለክቶ ከሚገኘው ውጤት ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ የአልኮል ጥንካሬውን ለመለካት ማናቸውንም ዜደ ለመጠቀም ይችላል:-

ሀ) ወካይ የሆነ ናሙናን በመውሰድ በተፈቀደው ዘዴ መሰረት ዝቃጭንና ጋዝን በማውጣት የተወሰነ መጠንን በ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀት ካልሲየም ሀይድሮክሳድ ጨምሮ በማጣራት አልካሊን በማውጣት፣

ለ) የማጣራቱ ስራ ከመከናወኑ በፊት የነበረው መጠን ሳይለወጥ በተጣራ ውሃ በ20 ዲግሪ ሲንቲግሬድ አልኮሉን በመለካት፣

ሐ) በተፈቀደ የፒክኖሜትር ልኬት መሰረት በአየር ውስጥ የሚኖረው ክብደት ከ20 ዲግሪ ሲንቲግሬድ መሆኑን ማረጋገጥ በሚቻል አኳኋን የተጣራው አልኮል ጥንካሬ የተለካ ከሆነ፣

መ) በፀደቀ የአልኮል ላቦራቶሪ ስንጠረዥ መሰረት የምርቱ የአልኮል ጥንካሬ በተወሰነ መጠን አልኮል በመቶኛ ሲለካ በዚህ ዘዴ የአልኮሉ ክብደት በስንጠረዥ ከሰፈሩ ሁለት አጋዞች መካከል ከሆነ የአልኮሉ ጥንካሬ በሊንየር ኢንተርፖሌሽን ይወሰናል።

33. የአልኮል ጥንካሬ መለካት - ከፍተኛ የአልኮል መጠን ያላቸው

1) የአልኮል መጠን መለካት ያለበት በአውቶማዩል ዴንሲሜትር ነው። የሚከተሉት ሁለት መስፈርቶች ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል።

ሀ). ጥንካሬው መለካት ያለበት በባዶ በሚኖረው ክብደት ሳይሆን በአየር ውስጥ በሚኖረው ክብደት ሲሆን

በመጨረሻው በአየር ውስጥ ወደ ሚኖረው ክብደት መለወጥ ይኖርበታል።

ለ). ልኬቱ በሚከናወንበት ጊዜ የፈሳሹ ሙቀት 20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ልኬቱ በተለያየ

ሙቀት መከናወን የሌለበት ሆኖ፣ በመጨረሻም ከ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ጋር ተመጣጣኝ ወደ ሆነ

ክብደት መቀየር ይኖርበታል።

2) አውቶማቲክ ዴንሲሜትር በመጠቀም በትክክለኛ እና በእርግጠኝነት ክብደቱ መለካት አለበት።

3) ከአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ውጪ የሆነ ሌላ የመለኪያ መሳሪያ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ፣ ይህ ዘዴ በኤክሳይዝ ፈቃድ ላይ መመልከት ያለበት ሲሆን፣ ትክክለኛነቱ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት መረጋገጥ አለበት።

ክፍል አስር

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከተፈቀደለት ፋብሪካ ስለማውጣት

34. ሽያጭ ከተከናወነ በኋላ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ስለማውጣት

1) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችን ከፋብሪካው እንዲወጣ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል።

2) በታወቀ ሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ የወጡ ዕቃዎች የገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማሰረከቢያ ሰነድ እና የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥባቸው ይገባል።

3) ወደፊት ሽያጫቸው የሚከናወን ዕቃዎች ካልሆኑ በስተቀር ከፋብሪካ በሽያጭ በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት የሽያጭ ደረሰኝ መቆረጥ አለበት።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህጋ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

4) ከተፈቀደለት ፋብሪካ ከወጡ በኋላ የሚሸጡ ዕቃዎች ከፋብሪካው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለደንበኛው ተሸጠው የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥላቸው እና ሽያጩ ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር እንዲጣጣም መደረግ ይኖርበታል።

35. ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ ስለሚወጡ ዕቃዎች

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ሽያጭ የሚከናወነው ከፋብሪካው ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ለሽያጭ እንዲውሉ ከፋብሪካው በሚወጡበት ጊዜ የምርቱ ልዩ መጠሪያ፣ ዓይነት እና ብዛት የሚገልፅ የማስረከቢያ ሰነድ መዘጋጀት አለበት።
2) የማስረከቢያው ሰነድ በገቢዎች ቢሮ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል።
3) ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ የተሸጠውን ዕቃ ብዛት፣ ዓይነት፣ልዩ መጠሪያ፣ ለገቢዎች ቢሮ አሰቀድሞ የተገለፀውን ለኤክሳይዝ ታክስ መሰረት የሆነውን ዋጋ፣ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ልክ እንዲሁም የገዥውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድራሻ የሚያሳይ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ገዥ መሰጠት አለበት።
4) የሽያጩ ደረሰኝ ዕቃው ከፋብሪካ በወጣበት ጊዜ የተመዘገበውን የማስረከቢያውን ሰነድ ቁጥር መያዝ ይኖርበታል።
5) የሽያጭ ደረሰኙ ቅጂዎች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን፣ ዋናው ለደንበኛው ይሰጣል፣ቀሪው ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር ይያያዛል።
6) ከፋብሪካ የወጣውን፣ የተሸጠውን እና ተመላሽ የተደረገውን ዕቃ በትክክል ለማስታረቅ እንዲቻል በሽያጭ ደረሰኙ ላይ የማስረከቢያው ሰነድ ቁጥር እንዲሁም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ የሽያጭ ደረሰኙ ቁጥር መባፍ አለበት።

ክፍል አስራ አንድ

ጌጣጌጥ፣ጨውና የፕላስቲክ መያዣ

36. በጌጣጌጥ ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

1) የከበሩ ማዕድናትን (አልማዝ፣ወርቅ፣ብር እና) ወይም ኦፓል ወዘተ) በከፊል የያዙ ጌጣጌጦች የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጌጣጌጥነት ያልተሰራ ጥሬ የከበረ ማዕድን (አልማዝ፣ወርቅ፣ብር፣አፓል ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑት) የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልበትም።

3) በጌጣጌጥ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ጌጣጌጡ እንደተመረተ ይቋቋማል።

4) ለጌጣጌጥ አምራቾች ጥሬው የከበረ ማዕድን እንደጥሬ ዕቃ የቆጠራል።

5) የከበሩ ማዕድናትን (አልማዝ፣ወርቅ፣ብር፣አፓል ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ) የሚያመርቱ የማዕድን ኩባንያዎች ለኤክሳይዝ ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የለባቸውም።

6) ጌጣጌጥ የሚያመርቱ ድርጅቶች ያመረቱትን ጌጣጌጥ የሸጡበትን የማስረከቢያ እና የሽያጭ ሰነድ መያዝ አለባቸው።

7) የጌጣጌጥ አምራቾች በተፈቀደለት አምራችነት የመመዝገብ እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አለባቸው።

37. በጨው ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

1) ጨው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በመሆኑ ጨው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያመርት ሰው ይህንኑ ለገቢዎች ቢሮ ማስታወቅ አለበት።

2) የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት እና ለተለየ ዓላማ እንዲውል ለማድርግ በፋብሪካ የሚመረት ጨው በድጋሚ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልበትም።

38. በኘላስቲክ መያዣ ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

1) ለአዋጅና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም "የኘላስቲክ መያዣ" ማለት በዕቃ ማጓጓጥነት የሚያገለግል የኘላስቲክ ዘንቢል ሲሆን፣ የዕቃ ማሸጊያን አይጨምርም።

2) የኘላስቲክ መያዣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በማምረቻው ቦታ ሲሆን፣ በአዋጁ በተደነገገው መሰረት በኪሎግራም የተወሰነውን የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ በማድረግ ይሆናል።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀትና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

3) በማምረቻ ቦታው የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት የኘላስቲክ መያዣ በዕቃ መያዣነት ከዕቃ ጋር ወይም ለብቻው በሚሸጥበት ጊዜ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ አይኖርም።

39. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1) ይህ መመሪያ አዋጁ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ እስከወጣበት ቀን ድረስ በነበረው አሰራር መሰረት ኤክሳይዝ ታክስ ሲከፍሉ የቆዩ ግብር ከፋዮች በነበረው አሰራር መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል።

40.<u>ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር የተያያዘ ሠንጠረዥ</u>

ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር የተያያዘው ሰንጠረዥ ተጣጥመው ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የሚያስችል ማብራሪያ እና የተለያዩ ቅጻ ቅጾች የገቢዎች ቢሮ ሊያወጣ ይችላል።

41. <u>መመሪያው የሚፀናበት ቀን</u>

1/ ይህ መመሪያ በቢሮ ኃላፊው ተፈርሞ ከወጣበት ከታህሳስ 2015 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለፀው ቢኖርም ይህ መመሪያ በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ አዲስ ቁጥር ከተሰጠው በኃላ የሚቋቋም መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በክልሉ ገንዘብ ቢሮ ድረገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባሕር ዳር
ታህሳስ 2015 ዓ.ም

ጥላሁን መሀሪ አንተነህ (ዶ/ር)
የገንዘብ ቢሮ ኃላፊ